# ዲሲ ውስጥ ታላቅ የተቃውሞ ሰልፍ በወያኔ ላይ ተካሄደ




ኢትዮጵያን ለማጥፋት ኢትዮጵያዊነትን ለማክሰም ላለፉት 35 ዓመት በቀንና በጨለማ እየተንቀሳቀሰ ያለው ወያኔ ሰኞ መጋቢት 17 ቀን 2004 ( March 26, 2012) በዋሽንግተን DC በተቃውሞ እሳት ተለብልቧል።



ተከብሮ የቆየውን የታሪካዊውን የዋልድባ ገዳም መሬት ለከበርቴዎችና ለባዕዳን በመሸጥ በሰፊው እንዲታረስ እያደረገ ያለውን እኩይና ሠይጣናዊ ሥራ በመቃወም ቁጥራቸው ከፍተኛ የሆነ ኢትዮጵያውያን በወያኔ ኤምባሲ በመገኘት ተቃውሟቸውን አሰምተዋል።



በአጭር ጊዜ ውስጥ ከዋሽንግተን አካባቢ ባሉ መንፈሳዊ ወጣቶች በተጠራው ሠልፍ ላይ የኢሕአፓ ወጣቶች ክንፍ ድርጅትና ባካባቢው የሚገኙ ፀረ ወያኔ የሆኑ የሬዲዮ አዘጋጆች፤ እንደ የኢትዮጵያዊነት ሬዲዮ አዘጋጅ፣ ሌሎች የወጣት ስብስቦች በተገኙበት ፀረ ወያኔው ሰልፍ በደመቀ ሁኔታ ተካሂዷል።



በፀሎት የተጀመረው ዝግጅት የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የተገኙበት ሲሆን ውስጣዊ አንድነቱን አረጋግጦ ውሏል። ከጠዋቱ በሶስት ሰዓት (9am) በተጀመረው ሰልፍ ላይ ወያኔ የዋልድባ መሬት በኃይልና በማን አለብኛነት መቀማቱን፤ በአሰቦትና በዝቋላ ገዳማት ላይ የደረሰውን ቃጠሎ በመኮነንና በእነ መለስ ዜናዊና በእነ አባ ጳውሎስ ጣምራ የዘር ትሥሥር ኢትዮጵያዊነት አይጠፋም በማለት ነበር ወጣቶቹ

የኢትዮጵያን ሕዝብ ብሶት ሲገልጹ ያረፈዱት። በስደት ከሚገኘው ህጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ የተዘጋጀውን የተቃውሞ ደብዳቤ አባቶች ከሰልፉ አዘጋጆች ጋር በመሆን በኢምባሲ




ለሚገኙት የወያኔ ባለስልጣኖች ለመስጠት ያደረጉት ሙከራ በወያኔው ግርማ ብሩ ትእዛዝ



ሰጭነት በአንዱ የወያኔ ወዝ አልባ ዘበኛ ከልካይነት ሊሳካ ሳይችል ቀርቷል። ወያኔ ምን ጊዜም ቢያጥቡት የማይጠራ ቢያሰጡት የማይደርቅ ነውና።

ሰኞ ዕለት የዋልድባን ገዳም መደፈር በመቃወም  በስፍራው በመገኘት ሰልፍ የወጣው ኢትዮጵያዊ የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ብቻ ሳይሆኑ በርካታ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞችም በስፍራው ተቃውሟቸውን ሲያሰሙ መስተዋሉ የጥያቄው ኢትዮጵያዊነት የጠነከረ መሆኑን ያሳያል።

በመጨረሻም በኃይላችን አንመካምና ሌሎችም መንፈሳዊ መዝሙሮችንና በመዘመር ሞት




ለወያኔ፣ ሞት ለመለስ፣ ሞት ለበረከት ፣ ሞት ለአባ ገብረመድህን የሚሉትንና ሌሎችንም መፈክሮች በማሳማት ተቃውሞ ከተሰማ በኋላ  የመንፈስ አባቶች ቡራኬ ሰጥተው የሰልፉ ፍጻሜ ሆኗል።

ከዚህ ሰልፍ በኋላም በሰልፉ ላይ ከወገን ኢትዮጵያውያን በቀረበው ጥሪ መሠረት በሳዑድ አረቢያ ለሚሰቃዩ ወንድምና እህቶች ተቃውሞና ብሶት ለማሰማት እዚህ የነበረው ስልፈኛ በሳዑድ አረቢያ ኤምባሲ ፊት ለፊት በመገኘት ብሶቱን ሲያሰማ ቆይቷል። ወያኔ ከሳዑድ አረቢያ ጋር ኢትዮጵያን የሚያፈርስ የጥቅም ግንኙነት ያላቸው በመሆናቸው የሳዑዲ ኤምባሲ ተጠሪዎች ወጥተው  ስልፈኛውን ለማነጋገር ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል።

ትግላችን ይቀጥላል

ወያኔ ይጠፋል